# በሰላም ሚኒስቴር

## የሰላም እሴት ግንባታ ዳይሬክቶሬት ተሻሽሎ የተዘጋጀ

## የሰላም ክበባት ማቋቋሚያ መመሪያ

ጥቅምት 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## 1. መግቢያ

ሰላም ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 ከተሠጡት ተግባራት መካከል በክልሎች መካከልና በክልሎች ውስጥ የሚነሱ አለመግባባቶችን ፖለቲካዊ መፍትሔ እንዲያገኙ የማመቻቸትና በዘላቂነት እንዲፈቱ ድጋፍ በማድረግ ግጭቶች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ጉዳቶች በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ነው፡፡ የሰላም እሴት ግንባታን በሕብረተሰቡ ወስጥ በማስረጽና በማስፋት ግጭቶች ተከስተው ጥፋት ከማድረሣቸው በፊት የመከላከል ሥራ ማከናወን፤ አለመግባባቶችን በውይይት የመፍታት ባህል ማዳበር፣ ሁከትና ብጥብጥን የሚጠየፍ ማሕበረሰብ መገንባት ዋና ተግባር ሆኖ እየተሰራበት ይገኛል፡፡

የሰላም ሚ/ር የሰላም ክበባትን በማቋቋም የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ግጭቶች ተከስተው ጥፋት ከማድረሣቸው በፊት የመከላከል ሥራ በማከናወን ሁከትና ብጥብጥ የሚጠየፍ ማሕበረሰብ ለመፍጠር የሰላም ባህል  ግንባታን በሕብረተሰቡ የማስፋት ሥራ እንደዋነኛ ተግባር በመያዙ

የሰላም ባህል ማለት የአንድ ሕብረተሰብ ጠቃሚ እሴቶች ስብስብና የአኗኗር ዘይቤ ሲሆን፣ በዋናነትም መልካም የባሕሪ ለውጥ በማስረጽ ሁከትና ብጥብጥን በመከላከል በሕዝቦች መካከል ተከባብሮና ተቻችሎ አብሮ የመኖር ባሕልን የሚያዳብር በመሆኑና ያለመግባባቶችም በምክክርና በመደማመጥ የሚፈቱበት ጠንካራ የሰላም ማሕበረሰብ የሚገነባበት ሂደት በማስፈለጉ

የሰላም ባሕል ግንዛቤን ለተማሪዎች ለማስረጽ የሰላም ክበባትን በት/ቤቶች ውስጥ በማቋቋም እና ተማሪዎች የሰላም እሴቶችን እንዲላበሱ በማድረግ ከመምህራኖቻቸው ከቤተሠቦቻቸው እንዲሁም ከአካባቢው ነዋሪ ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት የሰላም ክበባት መርሆዎችና እሳቤዎችም እንዲያንፀባረቁ የሚያስችል አደረጃጀት በማስፈለጉ

ሀገራችን ኢትዮጵያም የአያሌ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንዲሁም የተለያዩ ኃይማኖቶች ተቻቸለው የሚኖሩባት ሀገር በመሆኗ እና ተማሪዎች ልዩነቶችን በውይይት

መፍታት፣ መከባበር፣ መቻቻል፣ እንዲሁም ከፍተኛ የሠላም ክህሎትና በጎ ማህበራዊ አመለካከት እንዲያዳብሩ የሠላም ክበባቱ አስተዋፅኦ ወሣኝ በመሆኑ

ለግብ ስኬታማነት የሚረዱና የችግር ፈቺነት ባህሪ የሚያላብሱ አላማዎች በት/ት ተቋማት ውስጥና ከት/ት ቤት ውጭ በሚከናወኑ ልዩ ልዩ ተግባራት መዳበር ስለሚገባቸው የሠላም ክበባትን በመላው የሀገሪቱ ት/ቤቶችና ከፍተኛ የት/ት ተቋማት ውስጥ ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ የሁሉም የት/ት ቤት ማህበረሰብ አባላትና የአካባቢው ሕብረተሰብ ጥረት ሲታከልበት ግጭቶች እንዲከሰቱ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ባሕላዊና ልማዳዊ ሥርዓቶችና አስተሳሰቦች እየተወገዱ የሠላም ግንዛቤ ያለው መልካም ዜጋን የመፍጠር ዋነኛ አላማ እውን ለማድረግ ይህ የሰላም ክበባት መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

- ይህ መመሪያ የት/ ቤት የሰላም ክበብ ማቋቋሚያ መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችለል፡፡

## 2. ትርጓሜ

2.1 የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር ት/ቤት ማለት በሁሉም ሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ የመንግስት ት/ቤቶች ናቸው፡፡

2.2 የሰላም ክበብ ማለት በት/ቤት የሰላም ባህልን ለመገንባት የተቋቋመ ክበብ ነው፡፡

2.3 የሰላም ቀን ማለት በየዓመቱ መስከረም 21 ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰላም ባህልን በመገንባት ዙሪያ የተከናወኑ ስራዎችን በመዘከር የሚከበር ቀን ነው፡፡

## 3. የክበቡ አስፈላጊነት

በት/ቤቶች ውስጥ የሠላም ክበባትን ማቋቋም ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት የሠላም ባህል ግንባታ ሥራዎችን በማከናወን ብጥብጥና ሁከትን የሚጠየፍ፣ ግጭቶችን/ ያለመግባባቶችን በውይይት የማፈታ እንዲሁም ሀገር ገንቢና ኃላፊነት የሚሰማው መልካም ዜጋ ለማፍራት ስለሚያስችል ነው ከነዚህም በተጨማሪም፡-

- ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የቀሰሟቸው ትምህርቶች እንዲሁም ከቤተሰብና ከሕብረተሰቡ የሚያገኟቸውን ጠቃሚ ባሕላዊ ፋይዳዎችን አዋህዶ የሠላም ባህል ግንዛቤ ለማስረፅና ለማጠናከር፣
- ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት አመለካከት ለማዳበር ሀገራችንን ካለችበት ችግርና ድህነት ለማውጣት የሚጥሩ ወጣቶችን ለማፍራት፣
- የተማሪዎችን ተሣትፎ በማሣደግ ለት/ቤት፣ ለመንግሥት፣ ለሕዝብ ሀብትና ንብረት የባለቤትነትና የተቆርቋሪነት ስሜትን እንዲያዳብሩ ስለሚያስችል፣
- ተማሪዎች በመቻቻልና ተከባብሮ ለጋራ ጥቅም መሥራት በተመለከተ የተሻለ ግንዛቤ በመያዝ፣ ተቀርጸው እንዲያድጉ ስለሚረዳና ተግባራዊ ዕውቀት ስለሚያስጨብጥ የሰላም ክበባትን በትምህርት ተቋማት ውስጥ ማቋቋም ከፍተኛ ፋይዳ አለው፡፡

## 4. የክበቡ ዓላማዎች

- ተማሪዎች ከሠላም ባህሎች የሚመነጩ ደንብና መመሪያዎችን አስፈላጊነትን ተገንዝበው በመልካም የሠላም ባህሎች በመታነፅ እሴቶችን በተግባር ላይ እያዋሉ እንዲያዳብሩና እንዲያሰፉ ማስቻል፣
- ተማሪዎች እርስ በእርስ፣ ከመምህራን፣ ከአስተዳደር ሠራተኞች እንዲሁም ከሕብረተሰቡ ጋር ያላቸውን መልካም ግንኙነት ማዳበር፣
- በትምህርት ቤት አካባቢ የሚታዩ ግጭቶች/ያለመግባባቶች እንዲሁም ጎጂ ልማዶችን ደረጃ በደረጃ ማስወገድ፣
- ተማሪዎች የመደማመጥ፣ የመከራከር፣ የመደራደርና ወደ እርቅ (Reconciliation) መምጣት የሚችሉበትን ሂደት በተግባር እንዲለማመዱ ማድረግ፣
- ከፍተኛ የሀገር ፍቅር ኖሯቸው በብሔር ብሐረሰብ እኩልነት የሚያምኑ፣ ለሀገር ሀብትና ንብረት ተቆርቋሪ ትውልድ እንዲሆኑ ማስቻል፣
- የዲሞክራሲያዊ መርሆዎችን መላበስ፤

## 5. የክበቡ እሴቶች

- መቻቻል
- ፍትህና ፍትሃዊነት (Justice & equity)
- እኩልነት
- ገለልተኝነት (Neutrality)
- በአጋርነት መሥራት

- ግልፀኝነትና ተጠያቂነት
- አሳታፊነት
- የዲሞክራሲያዊ መርሆዎችን መላበስ፣ መተግበርና ዘብ መቆም፣

# ክፍል ሁለት

## 1. ክበቡ የሚቋቋምባቸው የትምህርት ተቋማት

i. በአንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ሣይክል ትምህርት ቤቶች (ከ5ኛ - 8ኛ)

ii. በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ከ9ኛ - 10ኛ)

iii. በመሠናዶ ትምሕርት ቤቶች (ከ11ኛ - 12ኛ)

## 2. የክበቡ ኃላፊነትና ተግባር

የክበቡ አጠቃላይ ኃላፊነትና ተግባር ከላይ በተዘረዘሩት እሴቶችና መርሆዎች ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

- የክበቡን የሥራ አስፈፃሚ አካላት በዲሞክራሲያዊ መንገድ መምረጥ፣
- ሀገር አቀፍ የሠላም ክበብ መመሪያ መነሻ በማድረግ በት/ቤት ደረጃ የክበቡን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ አዳብሮ ማዘጋጀት፣
- ዓመታዊ እቅድ የመንደፍ፣ የማፅደቅና ተፈፃሚነቱን የመገምገም፣
- አባላት የመሪነት ሚና እንዲኖራቸው ድጋፍና ስልጠና መስጠት፣
- በወረዳ ደረጃ በሚዘጋጀው ዓመታዊ የት/ቤቶች የሰላም ክበባት ኮንፈረንስ ላይ መሳተፍ እና ከሌሎች ት/ቤቶች ክበባት ጋር የልምድ ልውውጥ ማካሄድ፣
- በሕብረተሰቡ የሚዘወተሩ ጠቃሚና ጎጂ ባህሎችን በመለየት የሰላም ባህሎችን ማዳበር የሠላም ተፃራሪ ባህሎችን ማስወገድ፣
- ተማሪዎች ከመምህራን፣ ከት/ቤቱ አጠቃላይ ማህበረሰብ ከወላጆቻቸውና ከህብረተሰቡም ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በመልካም ሥነ-ምግባር ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ማድረግ፣
- በት/ቤቱ ውስጥ የሚታዩ አለመግባባቶችን፣ ጎጂ ልማዶችንና ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊቶችን እንዲወገዱ ማድረግ፣

- የሰላም እሴቶችንና መርሆዎች በሕብረተሰቡ ውስጥ በማስረፅና በማስፋፋት በሥነ ፅሁፍ፣ በድራማና በፖናል ውይይቶችና የመሳሰሉት በማዘጋጀት ትምህርት መስጠት፣
- ህብረተሰቡን በማሳተፍ አርዓያነት ያላቸውን የእርቅ ሥራዎች (Reconciliation) መስራት፣
- በት/ቤቱ ውስጥ ዓመታዊ የሰላም ቀን በዓል ማዘጋጀት፣ የሰላም አርአያ የሆኑ ተማሪዎችና መምህራን ሽልማት መስጠት፣
- በት/ቤቱ ውስጥ በተከታታይ የሚሠጡትን የሰላም እሴት የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችን ተማሪዎች በየቤታቸው ለወላጆቻቸው የሚያስተላልፉባቸውን መንገዶች መቀየስ፣
- የተሻለ ግንዛቤ ያላቸውን ተማሪዎች በመመልመልና በማሠልጠን የአካባቢዎቻቸውን ሕብረተሰብ ግንዛቤ እንዲያስጨብጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

# ክፍል ሦስት

## 1. የክበቡ አደረጃጀት

- የት/ቤቱ የሠላም ክበብ የአባላቱን ጠቅላላ ጉባኤና የሥራ አስፈፃሚ አካላትን አካቶ ይደራጃል
- ጠቅላላ ጉባኤ ማለት በሠላም ክበብ ለመሳተፍ የተመዘገቡትን የክበቡን አባላት በሙሉ ያጠቃልላል፡፡
- የክበቡ ሥራ አስፈፃሚ አካል ማለት በክበቡ ውስጥ ለመሳተፍ ከተመዘገቡት ጠቅላላ አባላት መካከል ክበቡን ለመምራት በቂ ፍላጎትና ተነሳሽነት ያላቸው 5 አባል ሲሆኑ ተጠሪነቱም ለክበቡ ጠቅላላ ጉባኤ ነው፡፡

## 2. የክበቡ ጠቅላላ ጉባኤ ተግባርና ኃላፊነት

ጠቅላላ ጉባኤው በት/ቤቱ ርእሰ መምህር/ት (ምክትል ርእሰ መምህር/ት) የሚመራ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል

- የክበቡን መተዳደሪያና ደንብ ያፀድቃል፣ የሠላም እሴቶችን ባህሪ ሳያዛባ በአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት ተጨማሪና ማሻሻያ ማድረግ ይቻላል፡
- በደንቡ መሠረት የክበቡን ሥራ አስፈፃሚ አካላት ይመርጣል፣
- ለክበቡ ዓላማ ተግባራዊነት አጠቃላይ ስልት ይቀይሳል፣

- የክበቡን ሪፖርት ያዳምጣል፣ መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል፣
- የክበቡ እቅዶች በዓላማው መሠረት ስለመከናወናቸው ግልፅ ውይይትና ግምገማ ያካሂዳል፣
- ከኦዲተሮች የሚቀርቡ ዘገባዎችን አዳምጦ ስለ ክበቡ ሂሣብ አያያዝና የንብረት አጠባበቅ ውሳኔ ይሰጣል፣
- ከሥራ አስፈፃሚ አካላት ውስጥ ሴቶች እንዲካተቱ ተገቢ ድጋፍ ይሰጣል፣

## 3. የክበቡ ሥራ አስፈፃሚ አባላት

- 1/ ሰብሳቢ 2/ ፀሐፊ 3/ ገንዘብና ንብረት ያዥ 4/ የሒሣብና ንብረት ተቆጣጣሪ/ኦዲተር 5/ የክበቡ ተጠሪ መምህርት/ር

## 4. የክበቡ አባላት ስብጥር

- ተማሪዎች፣ መምህራን እንዲሁም የትምህርት ተቋማቱ ሠራተኞች የክበቡ አባላት መሆን ይችላሉ ፡፡

## 5. የክበቡ አባላት ብዛት

- የክበቡ አባላት ብዛት ገደብ የለውም

## 6. የክበቡ አባላት መብትና ግዴታ

የክበቡ አባላት የሚከተሉትን ዝርዝር ግደታዎች መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

- የህብረተሰቡን ጠቃሚ ልምዶች፣ ወጎች፣ ባህሎችና እንዲሁም የሠላም ክበብ እሴቶችና መርሆዎችን የመገንዘብ/መረዳት
- ሁሉንም ተማሪዎች በእኩል የማየትና የማገልገል፣
- በት/ቤቱ ውስጥ የሚታዩ አለመግባባቶች /ግጭቶች/ ሲከሰቱ ለማንም ወገን ሳይወግኑ በሰከነ መንፈስ የማስታረቅ፣
- ከደባል ሱስና ከሌሎች የዲስፕሊን ጉዳዮች እራስን ነፃ በማድረግ ለሌሎች አርአያ መሆን፣

# ክፍል አራት

## 1. የክበቡ ሥራ አስፈፃሚ ተግባርና ኃላፊነት

- ከጠቅላላ ጉባኤ ቀጥሎ ክበቡን በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል
- የክበቡን የአሠራር ስልቶች ይቀይሳል ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል

- በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡ ውሣኔዎችን ይፈፅማል ሌሎች ስራዎችንም ያከናውናል
- ልዩ ልዩ ንዑሣን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል አሠራራቸውንም ይመራል፣ ይቆጣጠራል
- ለጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች ሪፖርቶችንና አጀንዳዎችን ያዘጋጃል
- የክበቡን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ከት/ቤት አስተዳደር ጋር ይወያያል ከሌሎች ክበባት አመራሮችም ጋር ተባብሮና ተቀናጅቶ ይሠራል
- ተማሪዎች በጥናትና በምርምር እንዲሳተፉ ከት/ቤቱ አስተዳደር ጋር ጥረት ያደርጋል፣ ውጤቱንም ለአባላቱ ይገልፃል
- ከት/ቤቱ አስተዳደር ጋር በመሆን ለክበቡ ገቢ ማስገኛ ስልቶችን ይቀይሣል
- በየ15 ቀኑ በመሰብሰብ የተሠሩ ሥራዎችን ይገመግማል፣ ወደፊት ስለሚከናወኑ ሥራዎችም አቅጣጫ ይቀይሳል፡፡

## 2. የክበቡ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

ሰብሳቢው/ዋ ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

- የሥራ አስፈፃሚ ስብስባ በሰብሳቢነት ይኖሩታ/ይኖሩዋታል፣
- የሥራ አስፈፃሚ ውሣኔዎችን ያስፈፅማል፣
- የሥራ አስፈፃሚ አባላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይከታተላል እገዛም ያደርጋል፣
- የክበቡንና የሥራ አስፈፃሚውን አካል የሥራ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከመደበኛ ስብሰባ ውጭ የሥራ አስፈፃሚውን ለአስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል፣
- በክበቡ ስር የሚዋቀር ንዑሣን ኮሚቴዎችን ያሰተባብራል፣
- በጠቅላላ ጉባኤውና በሥራ አስፈፃሚው የታመነባቸውን ሌሎች ተግባራትን ያስፈፅማል፣

## 3. የፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

ፀሐፊ ተጠሪነቱ/ቷ ለሰብሳቢው ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነት ይኖሩታል

- የክበቡን የአስተዳደር፣ የፅሕፈትና የፋይል መዛግብት በኃላፊነት ትይዛለች/ይይዛል፣
- የክበቡን ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ትይዛለች/ይይዛል፣
- ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ተክታ ትሠራለች/ይሠራል፣

- ሪፖርቶችን ታዘጋጀላች/ያዘጋጃል፣
- በሰብሳቢ የሚሰጡ ሌሎች ሥራዎች ደርባ ታከናውናለች/ያከናውናል፣

## 4. የስብሰባ ጊዜ

- ጠቅላላ ጉባኤው በወር አንድ ጊዜ ይሠበሰባል፡፡
- ምልዓተ ጉባኤ ከክበቡ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ከአንድ ሁለተኛ በላይ የሚሆኑት አባላት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ጠቅላላ ስብሰባ ሊካሄድና ውሳኔዎች ሊተላለፉ ይችላሉ፡፡

## 5. የክበቡ ተጠሪ መምህርት/ር ተግባር ኃላፊነት

ተጠሪነቱ/ተጠሪነቷ ለሥራ አስፈጻሚው ሆኖ

- ስለ ሠላም እሴት ግንባታ ተከታታይነት ባለው መልኩ ግንዛቤ ማስጨበጫ መንገዶችን መፍጠርና ተማሪዎችን ማብቃት፣
- ጠቅላላ ጉባኤና ሥራ አስፈፃሚ የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን በመከታተል ከሥራ አስፈፃሚ ጋር የክበቡን ዓላማ ያስፈፅማል፣ ክበቡንም ለማጎልበት ከሥራ አስፈጻሚው ጋር ልዩ ልዩ ተግባራትን በማቀድ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣
- አለመግባባቶች ከተከሰቱ በውይይት የሚፈታበትን መንገዶች ይፈጥራል፣
- የክበቡ ዓላማዎችና እቅዶች ከት/ቤቱ ውጪ ስለሚሰሩበትና ውጤታማ ስለሚሆንበት ሁኔታ ከት/ቤቱ አስተዳደር ጋር በመወያየት ይሠራል፣

## 6. የክበቡ ስራ አስፈፃሚ ተማሪዎች እና መምህር/ት መምረጫ መስፈርት

- ለሰላም ክበብ መቋቋምና እንቅስቃሴ ፍላጎትና ተነሣሽነት የላት/ው
- በተማሪዎችና በት/ቤቱ ሕብረተሰብ ተቀባይነት ያለው/ት
- የት/ቤቱን ደንብና ሥርዓት የምታስከብር የሚያስከብር
- መልካም አርአያነት ያለው/ት
- የማስተባበርና የመሪነት ችሎታ ያለው/ት

# ክፍል አምስት

## ክበቡ ከሌሎች ክበቦች ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

በት/ቤት ውስጥ የተቋቋሙ የተለያዩ ክበባት የት/ቤት ማህበረሰብንና ተማሪዎችን በአመለካከት፣ በተግባር እና በክህሎት ለማዳበር እንዲያግዙና በትምህርት ከሚያገኙት ዕውቀት ተጨማሪ ልምዶችን በመቅሰም ለሀገርና ለወገን የሚጠቅሙ ዜጐች አድርጐ ለማፍራት ታስቦ ነው፡፡

## 1. ከስነ-ዜጋና ስነ-ምግባር ክበብ ጋር የሚኖረው ግንኙነት

በት/ቤቶች የሰላም ክበባትን በማቋቋም ተማሪዎችና የት/ቤት ማህበረሰቦችን የሰላም ባህልን እንዲያዳብሩ፣ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችንና ግጭቶች ተባብሰው ወደ ሁከት እንዳያመሩ በውይይት የመፍታት፣ ባህልን እንዲያዳብሩ በማሰልጠን ወደ ሥራ ማስገባት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ የክበቡ እሴቶችና ተግባራት ከስነ-ዜጋና ከስነ-ምግባር ክበብ ጋር የመመሳሰል ባህሪያት ስላሉት በአንድ አንድ አካባቢዎች ጥያቄዎች እንዲያነሱ ምክንያት ሁኗል፡፡ ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በሚዘረዘሩ ተግባራት ዙሪያ በጋራ ቢሰሩ የተሻለ ይሆናል፡፡

- በት/ቤት ውስጥ ተማሪዎች ከመምህራን ጋር ሰላማዊ ግንኙነት በመፍጠር፣ ለሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት አስተዋፅኦ በጋራ እንዲያበረክቱ አቅዶ መሥራት፣
- በመብቶችና በስነ-ምግባር ዙሪያ በሚደረጉ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች በጋራ ማካሄድ፣
- በት/ቤት በሚከበሩ በዓላት የሰላም ቀን፣ የብሔር ብሔረሰቦች ቀን፣ የባንዲራ ቀን …ወዘተ በስነ-ጽሑፍ፣ በድራማ፣ መዝሙር  እና የፖናል ውይይቶችን በማዘጋጀት የት/ቤት እና የአካባቢውን ማህበረሰብ ግንዛቤ ማሳደግ፣
- የሁለቱም ክበብ ተጠሪ መምህራን በተቻለ መጠን በጋራ አቅደው እንዲሰሩ የት/ቤት ርዕሰ መምህራን እገዛ ያደርጋሉ፣
- እንደ ት/ቤቱ ተጨባጭ ሁኔታ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ክበባት ጋር ሊጣመር ይችላል

## 2. ከሌሎች ክበባት ጋር

ክበቡ በት/ቤት ውስጥና በት/ቤት ውጪ ከሚገኝ ሌሎች ክበቦች ጋር በት/ቤቱ አማካይነት ግንኙነት በመፍጠር የት/ቤቶችን የሰላም እንቅስቃሴ ለሕብረተሰቡ ማስተዋወቅና በት/ት ሥራ ውስጥ ሕዝቡ ንቁ ተሣታፊ እንዲሆን ሁኔታዎችን በማመቻቸት፣

- የአካባቢን፣ የክልልን፣ የአገር አቀፍና ዓለም አቀፋዊ በዓላትን በጋራ በማክበር የሰላም ግንዛቤን መፍጠር፣

- በተለያዩ ወቅታዊና ማህበራዊ የሠላም ጉዳዮች ላይ የፓናል ውይይቶችን ኮንፈረንሶችን በማዘጋጀት ተማሪዎች የሠላም እሴት ግንዛቤ እንዲኖራቸው (peace talk program) ማድረግ፣
- በልዩ ልዩ የልማት እንቅስቃሴዎች መሳተፍ ለምሣሌ አካባቢን ማፅዳት፣ ችግኝ መትከል፣ በመንገድ ሥራ መሣተፍ ሌሎችም፣
- ከወላጆች ጋር ግንኙነት መስርቶ የሠላም ቀን የሠላም አምባሣደሮች ቀን በልዩ ልዩ ዝግጅቶች በማክበርና ህብረተሰቡንም ተሳታፊ በማድረግ የሠላም ግንዛቤን ማሣደግ፣

## 3. የት/ቤቱ አስተዳደርና ማህበረሰብ ከክበቡ ጋር ያለው ግንኙነት

ት/ቤቱና የት/ቤቱ ማህበረሰብ የሚከተሉትን ያከናውናል

- ክበቡን በሁሉም መልኩ ማጠናከር፣
- ተማሪዎቹ ንቁ ተሣትፎ እንዲያደርጉ ድጋፍ ይሰጣል፣
- ክበቡ በት/ቤቱ ውስጥና ከት/ቤቱ ውጪ ካሉ መሰል ሕጋዊ ክበባት እንዲሁም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ልዩ ልዩ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ፈጥሮ በእኩልነት እንዲሠራ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡
- የት/ቤቱ አቅም በሚፈቅደው መጠን ለክበቡ ልዩ ልዩ የማቴሪያል ድጋፍ የደርጋል፣ የመሰብሰቢያ ቦታዎችንም ያመቻቻል፣
- የት/ቤቱ ማህበረሰብ ስለ ሠላም እሴቶችና ስለ ክበቡ ዓላማ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በልዩ ልዩ የፓናል ውይይቶች ድራማዎችና የስነ ፅሁፍ ዝግጅቶች ወዘተ ላይ በመገኘት እንዲሳተፉ ከክበቡ አመራር ጋር የግንኙነት ስልቶችን ይቀይሳሉ፣

## 4. ክበቡ ከአካባቢው ሕዝባዊና መንግሥታዊ ተቋማት ጋር የሚኖረው ግንኙነት

- ከት/ቤቱ ውጪ የሚያደርገው ማንኛውም ዓይነት ግንኙነት በት/ቤቱ አስተዳደር በኩል ብቻ ይሆናል፡፡
- ከት/ቤት ውጪ መሰል ዓላማ ካላቸው ሕጋዊ ማህበራት ወይም በሕብረተሰቡ ውስጥ የሠላም እሴቶች ለማስረፅና ለማስፋፋት ልዩ ልዩ ውይይት፣ ድራማ የስነ ፅሁፍ መድረኮችን በጋራና በተናጠል በማዘጋጀት ይሠራል፣

- ሕብረተሰቡን በሚጠቅም ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ በሚያነሳሱ ሥራዎችና እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተሳታፊ በመሆን የሠላም እሴቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣
- ጉጂ የግጭት ባህሎችንና ልማዶችን በመከላከልና በማስወገድ ረገድ ሕጋዊ እውቅና ካላቸው ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሠራል፣
- በት/ቤት ግቢና ከት/ቤት ውጪ በልዩ ልዩ ሚዲያዎችና መድረኮች የስነ ፅሁፍ፣ ድራማና የፖናል ውይይቶች ወዘተ በመጠቀም የሠላም እሴቶች በሕብረተሰቡና በወጣቶች ዘንድ እየተስፋፉ እንዲጠናከሩ ጥረት ያደርጋል፣
- ከቀበሌ አስተዳደር፣ ከእድሮች፣ ከሴቶችና ወጣቶች ማህበራት …… ወዘተ ጋር ግንኙነት በማድረግ ይሠራል፡፡

# 5. ክበቡ ከአካባቢው የሰላም ኮሚቴዎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት

## 5.1 የክበቡና የሰላም ኮሚቴ የጋራ መድረክ

የት/ቤት ክበባት የሥራ አስፈጻሚዎች በት/ቤቱ አካባቢ ከሚኖሩ የሰላም ኮሚቴዎች ጋር የጋራ መድረክ ይፈጥራሉ፡፡

4.1.1 የሰላም ክበብ ከአካባቢው የሰላም ኮሚቴዎች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር የት/ቤት ርዕሰ መምህር/የወረዳ ት/ት ጽ/ቤት ኃላፊ ከወረዳ የቀበሌ የሰላም ኮሚቴ ሊቀ-መንበር አመራሮች ጋር በመሆን፣

- ለአስፈፃሚዎቹ የጋራ መድረክ መፍጠር
- የጋራ ዕቅድ እንዲያወጡና እንዲተገብሩ የክትትልና ድጋፍ ተግባራትን ያከናውናሉ

## 5.2 የጋራ መድረክ ተግባርና ኃላፊነት

- የት/ቤቶች የሰላም ክበባት እና የሰላም ኮሚቴዎች የመረጃ ልውውጥ ያደርጋሉ፣
- የአካባቢው ሕብረተሰብ የሀገር ሽማግሌዎችና ሌሎች ታዋቂ ግለሰቦችን በየት/ቤቶቹ ተገኝተው ልምዳቸውን ለተማሪው እንዲያካፍሉ የአካባቢው የሰላም ኮሚቴዎችም ሚናቸውን እንዲወጡ ማድረግ፣
- ተማሪዎች በሕብረተሰቡ ውስጥ ተሠማርተው የሰላም እሴት የግንዛቤ መስጫ ተግባራት ውስጥ እንዲሠማሩ ማድረግ፣

- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አለመግባባቶችና ግጭቶች ሲፈጠሩ በእርቅ ተግባራት ላይ በመሣተፍ እገዛ ማድረግ፣
- በጋራ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በመለየት የጋራ እቅድ ማውጣት፣

## 5.3 የጋራ መድረኩ የስብሰባ ጊዜ

- የት/ቤቶች የሰላም ክበባትና የአካባቢው የሰላም ኮሚቴዎች በየወሩ የጋራ ስብሰባ ያካሂዳሉ፡፡ ሆኖም እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ የስብሰባ ጊዜ ሊኖራቸው ይችላል፡፡

## 6. የሠላም ክበብ እቅድ አዘገጃጀትና አፈፃፀም

የክበቡ እንቅስቃሴዎች ትምህርታዊ፣ የሠላም መርሆችን የተላበሱና ውጤታማ እንዲሆኑ በእቅድ መመራት አለባቸው፡፡ እቅዳቸውም ተማሪዎችን፣ መምህራንን፣ የት/ቤቱን ሠራተኞችና ወላጆችን መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን አሳታፊ እንዲሆኑ ተደርገው መታቀድ ያለባቸው ሲሆን ይኸውም፡-

- ተማሪው ራሱንና ሀገሩን ከአስከፊ ድህነትና የኋላቀርነት አስተሳሰብ ለማላቀቅ የሚያስችል ዕውቀት ክህሎትና አመለካከት የሚያዳብርበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት፣
- ስለ ታቀዱት ሥራዎች አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች ምንነት ለተሣታፊዎች ማስገንዘብ፣
- የታቀዱት ሥራዎች መቼ? የት? በማን? እንዴት? ለምን? በምን? እንደሚከናወኑና ይዘታቸውን በዝርዝር መግለፅ፣
- የሚተገበሩ እቅዶችንም በክትትልና ግምገማ እንዲፈፀሙ ማድረግ፣

## 7. ለክበቡ መጠናከር በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ጽሕፈት ቤቶች ሚና

በትምህርተ ተቋማት የሰላም እሴት ክበባት እንዲቋቋሙ እና እንዲጠናከሩ ከክልል ትምህርት ቢሮዎች ጀምሮ በየደረጃው የሚኙ የትምህርት ጽ/ቤቶች ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡-

## 7.1 የክልል ትምህርት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

- ለክበቡ አላማ ተግባራዊነት አጠቃላይ ስልቶችን እንደ አስፈላጊነቱ መቀየስና ተፈጻሚነቱን መከታተል፣
- አቅም በፈቀደ መልኩ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግና የክበቡን ዘላቂ እንቅስቃሴ ማረጋገጥ፣

## 7.2 የዞን ትምህርት መምሪያ ተግባርና ኃላፊነት

- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ክበቡን አቅጣጫውንና አላማውን ጠብቆ እንዲሄድ ማስቻል፣
- አቅም በፈቀደ መልኩ ድጋፍ ማድረግና የክበቡ አባላት አቅምን ማጎልበት፣

## 7.3 የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊት

- በወረዳቸው ውስጥ ከ5ኛ ክፍል በላይ ባሉ ት/ቤቶች የተቋቋሙ የሰላም ክበባትን የተደራጀ ፋይል መያዝ
- የሰላም ክበባቱን ተግባርና ኃላፊነት መነሻ በማድረግ የእቅዳቸው ማካተት
- የክበባቱን ጠንካራና ደካማ ጐኖች በመለየት፣ ጠንካራ ጐኖችን በመቀመር ተሞክሮዎችን ማስፋፋት እንዲሁም ደካማ ጐኖችን በክትትልና ድጋፍ ሥራዎች ማስተካከል
- የክበቡን የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በወር፣ በሩብ ዓመት፣ በ6 ወርና በዓመት መለዋወጥ /ከወረዳ - ዞን - ክልል - ፌዴራል/
- የክበቡን አጠቃላይ እንቅስቃሴ መገምገምና ተፈጻሚነቱን ማረጋገጥ፣
- የክበቡን አጠቃላይ እንቅስቃሴ አቅጣጫ ማስያዝና ድጋፍ ማድረግ፣
- የሰላም ክበባት ከሰላም ኮሚቴ ጋር በጋራ የሚሠሩበትን መንገድ መቀየስ፣
- አቅም በፈቀደ መልኩ ልዩ ልዩ ድጋፍ ማድረግና የሥራ አስፈጻሚ አካላት አቅምን ማጎልበት፣
- ከሚመለከታቸው ሕጋዊ አካላት ጋር በመነጋገር ክበቡ የሚጎለብትበትን መንገድ ማመቻቸትና በጋራ የሚሠሩበትን አቅጣጫ መቀየስ፣

///